# Family Tax Benefit Part B (የቤተሰብ ታክስ ድጎማ ክፍል- ለ)



## Family Tax Benefit Part B—Amharic

ብቸኛ አሳዳጊ ወይም ሁለቱም ወላጆች በሚገኙባቸው ቤተሰቦች ውስጥ አንድ ዋንኛ ገቢ ኖሯቸው አንደኛው ወላጅ ግን በቤት ውስጥ ሆኖ ልጅን ለመንከባከብ ከመረጠ ወይም አንዳንድ ተባራሪ ስራ እየሰራ የማሳደጊያ ወጪን በከፊልም ቢሆን ለመሸፈን ለሚጥር ተጨማሪ እገዛ ይሰጣል።

Family Tax Benefit Part B (የቤተሰብ ታክስ ድጎማ ክፍል- ለ) የሚሰጠው የመጀመሪያና በሁለተኛ ደረጃ ገቢ የሚያስገኘው ሰው የገቢ መጠን መሰረት በማድረግ ታስቦ የሚከፈል ነው። ብቸኛ አሳዳጊዎች ሁልጊዜ የሚያገኙት ከፍ ያለውን የክፍያ ተመን ነው።

በየአስራ አምስት ቀኑ እንዲከፈልዎ የሚመርጡ ከሆነ በበጀት ዓመት ውስጥ የቤተሰብዎን የወደፊት ገቢ መገመት ያስፈልግዎታል። ከፈለጉም የ Family Tax Benefit Part B (የቤተሰብ ታክስ ድጎማ ክፍል- ለ) የዓመቱን ክፍያ በአንድ ላይ ተደምሮ በጥቅሉ ለመውሰድ ምምረጥ ይችላሉ። በየዓመቱ ቢከፈልዎት እላፊ ወይም ትርፍ ክፍያ ከመውሰድ ያድንዎታል።

## ይህንን ማግኘት የሚችለው ማነው?

የሚከተለውን ማሟላት አለብዎ፡

- ብቸኛ አሳዳጊ ቤተሰብ ከሆኑና የውላጅን የመጀመሪያና ሁለተኛ የገቢ መጠን መመዘኛን ካሟሉ፣ ወይም
- ሁለት አሳዳጊ ወላጆች ባለበት ቤተሰብ ከሆኑና የሁለቱም ወላጆች የመጀመሪያና ሁለተኛ የገቢ መጠን መመዘኛን ካሟሉ፣ እና
- ከመቶ 35 እጅ እንክብካቤ እራሱን ላልቻለ ህጻን የሚንከባከቡ ከሆነ፣ እና
- የቤተሰብ ድጎማ ክፍያ ሲባል የአውስትራሊያ የመኖሪያ ፈቃድን ማሟላት።
- ከመቶ 35 እና 65 እጅ የሚሆነውን ጊዜ እንክብካቤ ከሌላ ሰው ጋር ለህጻኑ የሚንከባከቡ ከሆነ፣ ታዲያ Family Tax Benefit Part B (የቤተሰብ ታክስ ድጎማ ክፍል- ለ) ክፍያን ለመካፈል ይችሉ ይሆናል።

ልጅዎን በጋራ የምታሳድጉ ከሆነ ልጁ በእርሶ ስር የቆየበት ጊዜ እየታሰበ የFamily Tax Benefit Part B (የቤተሰብ ታክስ ድጎማ ክፍል- ለ) ሊያገኙ ይችሉ ይሆናል።

## ምን ያህል ነው የማገኘው?

ሁሉም ተመን በ1/7/2008 ዓ.ም ወቅታዊ ነው።

የFamily Tax Benefit Part B (የቤተሰብ ታክስ ድጎማ ክፍል- ለ) ከፍተኛው ተመን እንደሚከተለው ነው፣

| የትንሹ ልጅ ዕድሜ | በየአስራ አምስት ቀኑ | በየዓመቱ (ከተጨማሪው) |
|---|---|---|
| ከ5 ዓመት በታች | $128.80 | $3,693.80 |
| ከ5-15 ዓመት (ወይም 16-18 ዓመት ሙሉ ሰዓት ተማሪ ከሆነ) | $89.74 | $2,675.45 |

## የገቢ መመዘኛዎች ምንድን ናቸው?

በአንደኛ ደረጃ ገቢ የሚያገኘው ሰው በዓመት $150,000 ዶላር ወይም ከዚያ በታች ሆኖ ከተገኘ ለብቸኛ ወላጅ እና ባለትዳር ለሆነ ቤተሰብ ለሚሰጠው አበል ማመልከት። ብቸኛ ወላጅ ለሆነ ቤተሰብ ከተፈቀደው የገቢ መጠን ገደብ በታች ከሆነ ሁልጊዜ ከፍተኛ መጠን ያለው የቤተሰብ ግብር ድጎማ ክፍል ለ ያገኛል።

ሁለቱም ወላጆች ባሉበት ቤተሰብ የሁለተኛ ገቢ ማስገኛ ምንጭ ፈተናን ተግባራዊ ሲሆን የዋና ገቢ ምንጩ በዓመት $150,000 ዶላር ወይም ከዚያ በታች የሚያገኝ ከሆነ ነው። በሁለተኛ ገቢ የሚያገኘው መጠን በዓመት $4,526 ዶላር ቢሆንም ከፍተኛ መጠን የቤተሰብ ግብር ድጎማ ክፍል ለ ክፍያን ያገኛል። በሁለተኛ ደረጃ ገቢ የሚያገኘው መጠን በዓመት ከ$4,526 ዶላር በላይ ከሆነ ታዲያ ክፍያው በሚያገኙት እያንዳንዱ ተጨማሪ ዶላር በ20 ሳንቲም ይቀንሳል።

We speak your language ✆ 13 1202

www.familyassist.gov.au

Australian Government
Family Assistance Office

ለሚፈቀድላቸው ወላጆች የሚያገኙት ገቢ መጠን ከሚከተለው በታች ከሆነ ጥቂት የቤተሰብ ግብር ድጎማ ክፍል ለ ማግኘት ይቻላል:

- የትንሹ ህጻን እድሜ ከ5 ዓመት በታች ከሆነ በዓመት $22,995 ዶላር፣ ወይም
- የትንሹ ህጻን እድሜ በ5 ዓመት እና በ8 ዓመት መካከል ከሆነ በዓመት $17,904 ዶላር

## የFamily Tax Benefit Part B Supplement (የቤተሰብ ታክስ ድጎማ ክፍል ለ ተጨማሪ) ማለት ምን ማለት ነው?

በየዓመቱ በFamily Tax Benefit Part B ተመን ላይ ተደምሮ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ እስከ $335.80 ተጨማሪ ሆኖ የሚሰጥ ክፍያ ነው። ይህም ተጨማሪ ክፍያ የሚሰጠው እርሶና የትዳር ጓደኛዎ በበጀት ዓመት ማብቂያ ላይ የታክስ ክፍያ ተመላሽ መጠይቅ በምታስገቡበት ተጠቃሎ የሚሰጥ ወቅት ይሆናል። እርሶና የትዳር ጓደኛዎ የታክስ ተመላሽ መጠይቅ ማስገባት የማይጠየቅባችሁ ከሆነ የFamily Assistance Office (የቤተሰብ ጉዳይ ርዳታ ሰጪ ጽ/ቤትን) ማሳወቅ አለባችሁ። Family Tax Benefit Part B Supplement (የቤተሰብ ታክስ ድጎማ ክፍል ለ ተጨማሪ) ክፍያ የሚሰጠው ቤተሰቦች እላፊ የወሰዱ ከሆነ ለዚያ ማጣጫ ታስቦ ነው።

## ወላጆች ወደሥራ ስለመመለስ

ከሐምሌ/July 7 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ ወላጆች ከወለዱ በኋላ ወደሥራ ከመመለሳቸው በፊት ለነበረው የበጀት ዓመት Family Tax Benefit Part B (የቤተሰብ ታክስ ድጎማ ክፍል ለ) ክፍያን ማግኘት ይችላሉ። እርስዎ ወይም ባለቤትዎ ከወለዱ በኋላ ወደሥራ ከተመለሱ፣ ታዲያ ለFamily Assistance Office (ለቤተሰብ ጉዳይ ርዳታ ሰጪ ጽ/ቤት) መናገር ያስፈልጋል።

## ተጨማሪ ማብራሪያ ማግኘት ከፈለጉ፣

- የFamily Assistance Office (የቤተሰብ ጉዳይ ርዳታ ሰጪ ጽ/ቤት) በስልክ ቁጥር 13 1202 ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ8.00am እስከ 5.00pm (EST) ባለው ሰዓት ውስጥ በመደወል በአማርኛ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።
- በድረገጻችን www.familyassist.gov.au ላይ ይገኛል።
- በአቅራቢያዎ የሚገኘውን Family Assistance Office በMedicare Australia መስሪያ ቤቶች፣ በCentrelink የባለጉዳዮች አገልግሎት ማእከሎችና በታክስ ጽ/ቤቶች መገበያያ ቦታ ላይ ያገኙታል።